# ሽብርና ግድያ የመብት ጥያቄን መገደብ አይችሉም !!!

*/በትግራይ ምዕራባዊ ዞን የዓረና ትግራይ አባል የነበሩ የሰላም ታጋይ አቶ ታደሰ አብርሃ መገደልን አስመልቶ በዓረና ትግራይ የተሰጠ ጋዜጣዊ መግለጫ /*

በትግራይ ክልል ምእራባዊ ዞን የዓረና ትግራይ የዞን ኮሚቴ አባል የነበሩ የሰላም ታጋይ አቶ ታደሰ አብርሃ ትናንት ሌሊት ማንነታቸው ባልታወቁ ሰዎች ታንቀው ለህልፈት ተዳረጉ ፡፡ታጋዩ ይህንኑ አደጋ ያጋጠማቸው ሰኔ 9 ቀን 2007 ዓ/ም ከምሽቱ 3 ሰዓት በሚኖሩበት በቃፍታ ሑመራ ወረዳ ማይ ካድራ በተባለው ከተማ ሲሆን የ 48 ዓመት ጎልማሳ ነበሩ ፡፡አቶ ታደሰ አብርሃ በ 1956 ዓ/ም በሕንጣሎ ወጀራት ወራዳ በማይ ነብሪ ከተማ ተወለዱ፡፡ ከ 1979 ዓ/ም እሰከ 1990 ዓ/ም በአሰብ ከተማ ሲኖሩ በኢትዮ ኤርትራ ግጭት ምክንያት በሻዕቢያ ግፈኛው መንግስት ከአሰብ ተባርረው ወደ ትውልድ ቀያቸው እንደተመለሱ ለስራ ፍለጋ ወደ ትግራይ ምዕራባዊ ዞን ቃፍታ ሑመራ ወረዳ ማይ ካድራ ከተማ ያቀኑት ፡፡ ወደ ማይ ካድራ ከተማ ከመጡ 10 ዓመት የሞላቸው ሲሆን በአከባቢው ነዋሪዎች የሚከበሩና ከማናቸውም አጉል ልምዶች የታቀቡ ነበሩ፡፡ የግል ማህደራቸው እንደሚያረጋግጠው አቶ ታደሰ አብርሃ ባለ ትዳርና የ 3 ቤተሰብ አስተዳዳሪ ነበሩ፡፡

አቶ ታደሰ አብርሃ የዓረና ትግራይ ፓርቲ አባል የሆኑት በ 20 -10 -2014 ዓ/ም ሲሆን በአባልነት በቆዩባቸው ጊዜ በተለይ የዓረና አባላት ከገዢ ፓርቲ ስውር ጥቃቶች ራሳቸውን እንዴት መጠበቅ እንደሚገባቸው በመምከር ይታወቃሉ፡፡ከምርጫው ማግስት ጀምሮ አልታገስ ያላችሁ የዓረና ትግራይ አባላት **ከምርጫው በኋላ እያንዳንዳቹህ ትለቀማላችሁ** የሚል ዛቻ በገዢው ፓርቲ ካድሬዎች ይደርሳቸው እንደነበረ በአከባቢው የቅርብ ሓላፊዎች ለሆኑት የዓረና ትግራይ አባላት ሪፖርት አድረገው ነበር ፡፡መኖርያ ቤታቸው የሚገቡት ሳይመሽ በገናው እነደሆኑ ቤት ያከራዩአቸው ሰው እና በቅርብ የሚያቁአቸው ሰዎች ይመሰክራሉ ፡፡ አደጋው እንዳጋጠማቸው በኪሳቸው የነበረው ገንዘብ እንዳልተወሰደ የተረጋገጠ ሆኖ ይህም የግድያው ምክንያት ሌቦች ወይም ዘራፊዎች ሊሆኑ እንደማይችሉ ነው ፡፡ከማንኛውም ጥል ወይም ቂም በቀል የሚባል አልነበረባቸውም ፤ለህልፈት በተቃረበች አንደበታቸው በ 3 የማይታወቁ ሰዎች እነደታነቁ መናገራቸው ተረጋግጦአል ፡፡ግድያው በከተማዋ ቀጠና 4 በተባለው አከባቢ ገድያ

እንዳልተፈፀመ አረጋግጫለሁ ይላል ፖሊስ ይህም ግድያው የተፈፀመው እጅግ ጥንቃቄ በተሞላበት እና በእንዲህ አይነቱ አገዳደል በሰለጠኑ ሰዎች መሆኑን ሁኔታው ያሳያል፡፡

ጉዳዩ ከፍተኛ የፀጥታ ስጋትን የደቀነ የወንጀል ድርጊት እያለና የማቹን የሬሳ ምርመራ በማድረግ የወንጀል ማጣራት ስራው የፖሊስ ሃላፊነት እያለ የማቹን ሬሳ ወደ ሆስፒታል የሚወስድ መኪና እንዲከራዩ ማሰገደድና የዓረና ፓርቲ አስተባባሪ የሆኑት አቶ መሰለ ገ/ሚካኤል መኪና ለመከራየት በድንጋጤ በሞተር ሳይክል ሲጣደፉ ምርመራውን የሚያካሂድ የፖሊስ ፅሕፈት ቤት ባልደረባ የሆነ ፖሊስ የሚጠቀሙበትን ሞተር ሳይክል በመያዝ በጠራራው ፀሃይ ብእግር እየተንከራተቱ መኪና እንዲፈልጉ ማስገደዱ የአከባቢው ፖሊስ ስራውን በአግባቡ አለመወጣቱ ብቻ ሳይሆን ፍትሕ ለሚፈልጉ የወንጀል ጉዳተኞች ፍትህን መንፈጉ የሚያመለክት ነው፡፡ የወንጀሉ ጉዳተኞች መኪና በመከራየት ማቹን በሁመራ ሆስፒታል ቢደርስም የህክምናው ምርመራ በተገቢው አለመካሄዱ የአብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ጡንቻ የሕክምና ሙያ ስነ ምግባርን ጭምር ማዳከሙ የሚጠቁም ሆኖ የተፈፀመው አሰቃቂ የግድያ ወንጀል ፖለቲካዊ ምክንያቱ የጎላ ያደርገዋል፡፡

የማቹ በሂወት የመኖር ህገ መንግሰታዊ መብት በቅጥር ነብሰ ገዳዮች ተነጥቆ ፣ አሰቃቂው የግድያ ወንጀል አንጥሮ በማጋለጥ ፍትህ የማግኘት መብት እንዳይከበርም ከላይ የተገለፀ የማድበስበስ ስራዎች እንደተካሄዱ የሚቹ ሬሳ ወደ ግድያው የተፈፀመበት ማይ ካድራ ከተማ ተመልሶ በሰኔ 10 ቀን 2007 ዓ/ም አቡነ አረጋዊ ቤተክርስትያን ከቀኑ በ 7፡30 የከተማው ነዋሪ በሞላ ሊባል በሚችል በተገኘበት መሪር ሃዘኑን የገለፀበት ስነስርዓት ቀብራቸው ተፈፅሞአል፡፡

ሽብርና ግድያ የመብት ጥያቄን የመገደብ አቅም እንደሌላቸው ያለፉት ስርአቶች አሳይተውናል ፣ ዓረና ከተመሰረተ ወዲህ ግልፅና ስውር ወከባ፣ከሰራ መፈናቀልና አስጊ ማስጠንቀቅያዎች ፣ ግልፅና ስውር ስለላና ክትትል --- ወዘተ ሁሌ የማይለዩን የህወሓይ/ኢህአደግ ችሮታችን ሆነው የግድያ ጉዳይ ከተነሳም በ 2002 አጠቃላይ ሃገራዊ ምርጫ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እጩ ተወዳዳሪ በነበረው የተፈፀመው የግፍ አገዳደል ፖለቲካዊ በመኖሩ በተራ ግድያ መከሰሱ የግድያ ተግባራቱ ፖለቲካዊ መሆናቸው የሚያመለክት ነው፡፡ የሁለቱም የግድያ አፈፃፀም ልዩነቱ የመጀመርያዊ ከምርጫው በፊት ሲሆን የአሁኑ ከምርጫው በሁዋላ መሆናቸው ሆኖ በተለይ የአሁኑ የአቶ ታደሰ አብርሃ ከምርጫ በኋላ የተፈፀመው ግድያ የተቃዋሚ ዓረና የምርጫ ታዛቢዎች ለምን እንዲበተኑ ተደረገ፣ድምፃችን የትገባ በማለት የጋለ ተቃውሞና

ቅሬታ በሚታይበት የትግራይ ክልል በመንቀሳቀስ የሚገኘው የዓረና ትግራይ ፓርቲ ቀጣይ ሰላማዊ ፖለቲካዊ ትግል ለማሸበር የታቀደ መሆኑን ሁኔታው ግልፅ ያደርገዋል፡፡ሆኖም የሰላም አማራጭ በሚያራምዱ የተቃዋሚ ፓርቲ አባላት ላይ ያነጣጠረ ግድያና የሽብር ተግባር ህወሓት / ኢህአዴግን የሰላም ሃይል ሳይሆን የነውጥና የጉልበት አማረጭ ሃይል ያደርገዋል ፣ የሃይል አማራጩ የሚከተሉ አሸባሪዎች እያለ ከፈረጃቸው ፓርቲዊች ልዩነት እንደሌለው በራሱ ተግባር ከማረጋገጥ አልፎ በማሸበርና በግድያ የሚታገስ የመብትና የነፃነት ጥያቄ የሌለ ስለመሆኑ ከራሱና ከታሪክ ሊማር አለመቻሉ እያስመሰከረ ይገኛል ፡፡

በዚህ አሳዛኝ አጋጣሚ ዓረና ትግራይ ለመላ የኢትዮጵያ ህዝቦች፣ ለትግራይ ክልል ህዝብ፣ በሃገር ውስጥም በሆነ በውጭ የሚንቀሳቀሱ ተቃዋሚ ዴሞክራሲያዊ ለውጥ ፈላጊ የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ ለሰብአዊ መብት መከበር የቆሙ ሀገር ማህበራትና ድርጅቶች  እንዲሁም ለመላው የዓለም ሕብረተሰብ የሚያስተላልፈው መልእክት ሁሌ የፖለቲካ ትኩሳት በማይለይበት በአፍሪካ ቀንድ የምትገኝ ሀገራችን እንዲህ አይነቱ የሽብር ተግባር ጦሱ ለክልል ትግራይ ወይም ለኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ለመላው ዓለም የሚተርፍ ጣጣ እንዳለው በመገንዘብ ተግባሩን ከምር እንዲኮንኑትና እንዲያጋልጡት ጥሪያችንን እናቀርባለን፣

በሃገር ውስጥና በውጭ ሃገራት የምትገኙ መላው የዓረና ትግራይ አባልና ደጋፊዎችም ግድያና ማሸበር የደካማ ፖለቲካዊ አማራጭ ማሳያዎች እንጂ የጥንካሬ መገለጫዎች እንዳልሆኑ በመገንዘብ ሰላማዊ ትግላችን አጠንክረን እንድንቀጥልበት ዓረና ትግራይ ጥሪውን ያስተላልፋል፣

የግፍ ግድያው ሰለባ የሆነው የሞራል ጠንካራው የሚች አቶ ታደሰ አብርሃ ቤተሰቦች እግዚአብሄር ፅናቱ እንዲቸራቸው የማቹ ነብስ እግዚአብሄር  በገነት በክብር ያሳርፍልን ዘንድ እንፀልያለን ፡፡

## ሽብርና ግድያ የመብት ጥያቄን መገደብ አይችሉም !!!

## ግድያና ሽብር የደካማ ፖለቲከኞች መለያ እንጂ የጥንካሬአቸው መገለጫ አይደለም !!!

## ሽብርና ግድያ የስልጣን እድሜ ሲሳጥሩ እንጂ የስልጣን እድሜ ሲያራዝሙ አልታዩም !!!